# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 165 ሃምሌ 7 2003 ገጽ 1


**በችጋር ለሚጠቃው ወገናችን መድረስ የምንችለው፤ የችጋሩ መሠረታዊ ምክንያት የሆነውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ አስወግደን ፍትህና ነፃነት የሰፈነባትን፤ ፈጠራ የተስፋፋባትን ኢትዮጵያን ስንገነባ ብቻ ነው። ጊዜ የለም .... ረሃብ ጊዜ አይሰጥም ። የወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ በአንድነት እንነሳ።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ግቡን እንዲመታ ኢትዮጵያውያን በአንድነት እንዲነሱ አነግና ግንቦት7 ጥሪ አቀረቡ

ባለፈው እሁድ ሃምሌ 3 ቀን 2003 ዓም በቨርጂኒያ አርሊንግተን ሸራተን ሆቴል ኢትዮጵያዊያን ባካሄዱት ስብሰባ ግንቦት ሰባት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ለእውነተኛ አንድነት የሚያበቃንን የዜግነት መብታችንን ለማስከበር ትብብር ወሳኝ ከሆነበት ምዕራፍ ላይ እንገኛለን ሲል የገለጸ ሲሆን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በበኩሉ የመለስ ዜናዊን ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝ ለመጣል ከምንግዜውም በላይ በመዘጋጀቱ በኦነግ ላይ ያለው ጥርጣሬ ተወግዶ ትግሉን በጋራ ለማራመድ ኢትዮጵያውያን በአንድነት እንዲነሱ ጥሪ አቅርቧል። በዚሁ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የተገኙት የኢኮኖሚክስ ምሁር ዶክተር ጌታቸው በጋሻው በበኩላቸው፡ የመለስ አስተዳደር ከየአቅጣጫው ቀውስ ላይ የሚገኝበት ወቅት መሆኑን በማመልከት የተቃዋሚዎች ትብብር ወሳኝ መሆኑን መናገራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

በዚሁ ስብሰባ ላይ የተገኙት የግንቦት ሰባት የነጻነትና የፍትህ ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ስለአንድነት ምንነትና አስፈላጊነት ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጋር በማያያዝ ሰፊ ትንተና ያቀረቡ ሲሆን አንድነታችን በአራት መሰረታዊ መገለጪያዎች ላይ የተደላደለ መሆኑን በመግለጽና እያንዳንዱንም መገለጫ በማብራራት ለተሳታፊዎች ንግግር አድርገዋል፤፤ ዶ ር ብርሃኑ የአንድነት አቀንቃኞች የአንድነትን አስፈላጊነት ለማስረዳት በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ስላለን ሚናችን ከተከላካይነት መውጣት አለበት ያሉ ሲሆን አንድነት ሲኖር ጠንካራ ሰላም ይፈጠራል፤አንድነት ትልቅ ሀገር ይፈጥራል፤ በዚህም ትልቅ ኢኮኖሚ እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ ለረሀብ የተጋለጠዉ ሕዝብ ቁጥር አሻቀበ፣ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ይፋ የተደረገው ቁጥር አሁንም ዝቅ ያለ ስለመሆኑ ስጋት እንዳለ ተገለጸ

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በኢትዮጵያ ለረሀብ የተጋለጠዉ ሕዝብ ቁጥር ወደ 4.57 ሚሊዮን ከፍ እንዳለ መግለጻቸው የታወቀ ሲሆን በኢትዮጵያ የዩናይትድ ስቴትስ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት / ዩ ኤስ አይ ዲ/ ዳይሬክተር ጂሰን ፍሬ-ይዘር የወያኔው ኢህአዴግ ባለስልጣናት የረሃብተኛዉን ቁጥር አሁንም ዝቅ አድርገዉታል የሚል ስጋት እንዳላቸዉ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል ያለዉ ሁኔታ ዝቅ ያለ ግምት የተሰጠዉ ሊሆን እንደሚችልና ይህም እንደሚያሳስባቸዉ መናገራቸው ታውቋል።

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት አደጋዉ በተከሰተበት የሶስቱ ሱማሊያ፤ ኢትዮጵያና ኬንያ አዋሳኝ ድንበር በኢትዮጵያ በኩል ያለዉን የረድኤት ተግባር ለመሸፈን በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ የተገለጸ ሲሆን በዚህ አዋሳኝ አካባቢ የሚገኘዉ ህዝብ አብዛኛዉ በከብት እርባታ እንደሚተዳደር ለማወቅ ተችሏል።

ኢትዮጵያዊያን በእንዲህ አይነት አሰቃቂ ሁኔታ በሚገኙበት ሰአት ላይ በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠር ዶላር በማውጣት ከሁለት መቶ በላይ ታንኮች መሸመቱን የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በአደባባይ ለአሻንጉሊቱ ምክር ቤት የገለጸ ሲሆን በሌላ በኩል በኦጋዴንና በሶማሌ ክልል የተለያዩ ቦታዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በአካባቢው መንቀሳቀስ የማይቹሉ በመሆናቸው ትክክለኛ የሆነውን የኢትዮጵያዊያን ረሃብተኞች ቁጥር ማወቅ እንዳልተቻለ ቀደም ብሎ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ የተሳሳተ ፖሊሲ የፈጠረው የዋጋ ግሽበት ባለፈው ወር ወደ 38 በመቶ ከፍ ማለቱ ተዘገበ

ሮይተርስና ብሉምበርግ በመባል የሚታወቁት የዜና አውታሮች ከትናንት በስቲያ ባወጧቸው ዘገባዎች በኢትዮጵያ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለው የዋጋ ግሽበት ባለፈው የሰኔ ወር ብቻ ወደ 38 በመቶ ማሻቀቡን የዘገቡ ሲሆን ለግሽበቱ ዋነና ምክንያትም በምግብ ዋጋዎች ላይ እየታየ ያለው ጭማሪ እንደሆነ የዘረኛው አገዛዝ የሚመለከተው ጽ ቤት መናገሩን ገልጸዋል። እንደ ታውቂ የዜና ምንጮቹ ዘገባ ይህ የታየው የዋጋ ግሽበት ባለፉት ዓመታት በሰኔ ወር ላይ ከታዩት የዋጋ ግሽበቶች አንጻር ሲታይ ደግሞ በ45 በመቶ ማደጉ ታውቋል።

የወያኔው አገዛዝ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጽ ቤት በተለይም በስንዴ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስጋ፣ ድንችና ሌሎችም የምግብ ሸቀጦች ላይ በመታየት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁልፍ ቦታዎችን ከአንድ ብሄር በተውጣጡ ግለሰቦች የማስያዝ ተግባሩን ከወታደራዊ ተቋአማት ወደ ሲቪክ ተቋአማት አዞረ

ዘረኛውና አምባገንኑ የወያኔ አገዛዝ በቅርብ ጊዜ አሰናበትኩዋቸው ካላቸው ወታደራዊ መኮንኖች ውስጥ በጀነራልነት ማእረግ የሚገኙትን በርካታ መኮንኖች በቴሌኮሚዩኒኬሽን መስሪያቤት ውስጥ ቁልፍ ናቸው የሚባሉ የስልጣን ቦታዎችን እንዲይዙ ማድረጉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

የውስጥ ምንጮችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን እንደገለጸው ቁልፍ የሚባሉት የቴሌ ኮሚዩኒኬሽን ጽ ቤት የስልጣን ቦታዎች ማለትም የኔት ወርክ ሴክዩሪቲ፤ የፊዚካል ሴኪዩሪቲና የፋይናንስ ክፍሎች የትግራይ ክልል ተወላጆች በሆኑት በነኝሁ የቀድሞ የህወሃት ታጋዮች እና ያለምንም ሥልጠና ለጀነራልነት የበቁ የመለስ ታማኞች መያዙ ታውቆአል። የኔት ወርክ ሴክዩሪቲ ክፍል የሞባይልና የኢንተርኔት ጠለፋ የሚካሄድበት ሲሆን፣ ፊዚካል ሴኪዩሪቲ ደግሞ አጠቃላይ የቴሌን መስሪያ ቤት ድርጂታዊ ጥበቃ የሚያከናውንበት ክፍል እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

ዘጋቢአያችን በቴሌኮሚዩኒኬሽን መስሪያ ቤት የሚሰሩ ምንጮችን በመጥቀስ እንደገለጸው፣ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ፋይናንስ ክፍሉም እንዲሁ አንድ የህዋሃት ታጋይ የተመደበለት ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ከፍራንስ ቴሌኮም ጊዚያዊ ስራ አስኪያጅ ጋር በመቀናጀት ድርጂቱን እየመራ ያለውም አንድ ከዚሁ ከትግራይ ብሄር የወጣ የመከላከያ ጀኔራል ነው። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአለታ ወንዶ ብጥብጥ ተከሰተ፣ ወጣቶች ወያኔ የጠራውን ስብሰባ ረግጠው ወጡ

የዘረኛው ወያኔ ኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራሜን ለማስረጽና ወጣቶችንም በአባልነት ለመመልመል እንዲሁም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት በሚል ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓም በአለታ ወንዶ ሊያደርግ አቅዶት የነበረው ስብሰባ በብጥብጥ መበተኑን ምንጮቹ ማስታወቃቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው የወያኔው ኢህአዴግ ከአሮሬሳ፣ ከበንታና ከአለታ ወንዶ ከተማዎች የተመረጡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ስራ ያጡ ሁለት ሺህ ወጣቶችን በቀን ለያንዳንዳቸው 50 ብር የውሎ አበል ይከፈላቸዋል በሚል ማባቢያ ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓም በአለታ ወንዶ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰብስቦ ጠርቶ ስለ አምስት አመት የልማት መርሃ ግብር ተብየው ና የትራንስፎርሜሽን ፕላን እንዲሁም በሃገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ለመስጠት ሞከሮ እንደነበረና ሳይሳካ እንደቀረ ለማወቅ ተችሎአል። ለስብሰባው አለመሳካት ዋናው ምክንያት የሆነው ተሰብሳቢዎች በቀን ሃምሳ ብር እንደሚከፈላቸው በአካባቢያቸው በሚገኙ ካድሬውች እንደተነገራቸው በመግለጽ ከስብሰባው በፊት የተነገራቸው የአበል ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውንና ስብሰባውን ሊመሩ የሄዱ የወያኔ ኢህአዴግ ሆድ አደሮችም፣ ከስብሰባ በሁአላ እንነጋገራለን በማለት ለማድበስበስ በመሞከራቸው ፣ ወጣቶቹ በተሰጣቸው መልስ በመበሳጨትና ሁሉም በአንድነት በመሆን የተለያዩ ቁአሳቁሶችን በመወርወር ከስብሰባው አዳራሽ ለቀው በመውጣታቸው ነው ተብሎአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ዘረኛው ወያኔ ኢትዮጵያዊያንን አሁንም እያሳደደና እያሰረ ነው፣ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ አርባ የሚሆኑ መምህራንና ሰራተኞች ታሰሩ

ከዛሬ ነገ ከስልጣን ወምበሬ እፈናቀላለሁ በሚል እንቅልፍ አጥቶ እየባነነ ያለው ወያኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጂምላ የሆኑ እስራቶችን በዜጎች ላይ መፈጸም የጀመረ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ የአዳማ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች የሆኑ 40 ሰዎችን አፍሶ ማሰሩን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ አባስተላለፈው ሪአፖርት ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት እነኝህ መምህራንና ሰራተኞች ለእስራት የተዳረጉት ለዘረኛው አገዛዝ ባላቸው ይፋ ተቃውሞ ሲሆን ዘረኛው ወያኔ ግን መምህራንና ሰራተኞችን ያሰርሁ ተማሪአዎች የሚመገቡትን ምግብ በመመረዛቸው ነው ማለቱ ታውቁአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በተለይም በትምህርት ተቋአማት ተማሪዎችና መምህራን ህዝባዊ አመጽን ይቀሰቅሳሉ የሚል ፍራቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደረበት በመምጣቱ ጭፍን የሆኑና እንዲህ አይነት እንቅስቃሴ የሚያሳይትንም ሆነ ሌሎችን ኢትዮጵያዊያን ለማሸማቀቅ የእስራት፣ ድብደንባና ሌሎች እንግሎቶችን ሲፈጽም እንደቆየ በስፋት መዘግባችን ይታወሳል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጸረ ሽብርተኝነት ህግ አርቅቂያለሁ ብሎ በአሻንጉሊቱ ፓርላማ ተብየ ካጸደቀ ወዲህ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን፣ በሽብርተኝነት የመወንጀልና የማሰቃየት ስራን ማከናወኑ ሲዘገብ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን ከኢትዮጵያዊያንም አልፎ ስዊድናዊ የሆኑ ዜጎችን ሳይቀር አሸባሪዎች ናቹሁ በማለት በዝብርተኝነት ህግ መክሰሱም በቅርቡ መዘገቡ ይታወቃል።

# ችጋር በቃን!!! ረሃብ በቃን!!! መለስ በቃን!!!

በወገኖቻችን ላይ አስከፊ ችጋር መጥቷል። ምሥራቅና ደቡብ ኢትዮጵያን በአስከፊ ሁኔታ እያጠቃ ያለው ጥልቅ መሠረት ያለው ችጋር እንጂ የአንድ ወቅት ረሃብ አይደለም:: ከአሁኑ ሰው በረሃብ መሞት መጀመሩ ከሁለትና ሶስት ወራት በኋላ የሚመጣውን አደጋ ከባድነት መገመት ይሰቀጥጣል።

- “ከ10% በላይ ተከታታይ እድገት አሳይተናል” የሚለው ዓይን ያወጣ ውሸት፣
- “ድህነትን ተረት እናደርጋለን” የሚለው ጉረኛ መፈክር፣
- የመለስ ዜናዊ ጀሌዎች በፎቅና ቪላዎች መንበሽበሽ፣
- የለም መሬቶች ለቻይናና አረብ ቱጃሮች መታደል፣
- የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ “የህዳሴ ብስራቶች”፣
- ወዘተ .... ወዘተ

ለህዝባችን ቁርስ፣ ምሳና እራት አልሆኑም።

መለስ ዜናዊ እንደለመደው ችግሩን በተፈጥሮ እና በለጋሾች ፈጥኖ አለመድረስ ማላከኩን ተያይዞታል።

- ለመሆኑ እየተደጋገመ ለሚመጣ ችጋርና ረሃብ ተፈጥሮ ብቻውን በቂ ምክንያት ሆኖ ያውቃልን?
- ለምንድነው ፍትህና ነፃነት በሰፈነባቸው አገሮች ውስጥ ዝናብ ጠፍቶ የእርሻ ምርት በከፍተኛ መጠን በሚቀንስበት ጊዜ ሰው በረሃብ የማይሞተው?
- አስከፊ የረሃብ ዜናዎች የሚሰማባቸው አገሮች በሙሉ ነፃነት የታፈነባቸው አገሮች መሆናቸውስ የአጋጣሚ ጉዳይ ነውን?
- ለምንድነው አንድ ዓይነት ችግር እየተደጋገመብን መላ መፈለግ ያቃተን? “ችግር የመሳካት እናት ናት” የሚለው ብሄል ምነው እኛ ዘንድ አልሰራ አለ?

ችግር የመሳካት እናት የምትሆነው በነፃነት ማሰብ የሚችል ጭንቅላት ሲኖር ነው። የኢትዮጵያ ገበሬና አርብቶ አደር ነፃነቱ ተገፎ እያለ እንደምን ችጋርን መቋቋሚያ መፍትሄ መፈለግ ይችላል?

ነፃነቱን የተገፈፈ ጭንቅላት ለችግሮች መፍትሄ የማፍለቅ አቅም የለውም። እንዲህ ዓይነቱ ጭንቅላት ችግሮችን ማሸነፍ ሳይሆን ተሸናፊነትን ተቀብሎ ከችግሮች ጋር ተስማምቶና ተወዳጅቶ መኖርን ይመርጣል። ለዚህም ነው የአስተዳደር በደልና ረሃብ ምክንያትና ውጤት ብቻ ሳይሆን እጅና ጓንትም ጭምር የሆኑት። ነፃነት ያለው ህዝብ ረሃብን እንደሚያሸንፍ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ረሃብን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ውጤት ብቻ አድርጎ ማቅረብ እውነትን መሸፈጥ የሚሆነው። ችጋርና ረሃብ የብልሹ አስተዳደር ውጤቶች ናቸው።

በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው ስር የሰደደ ችጋር፣ አገዛዝ በተቀየረ ቁጥር እየባሰበት የመጣው የብልሹ አስተዳደር ውጤት ነው። አገራችንን የችጋር ቀጠና ካደረጉ የ20 ዓመታት የመለስ ዜናዊ “የሸፍታ ኢኮኖሚ” ፓሊሲ ውጤቶች መካከል አንዳንዱን ለአብነት ያህል መዘርዘር ይቻላል።

1. በየጊዜው በሚፈነዳዱ ግጭቶች ሳቢያ አርብቶ አደሩ ተረጋግቶ ስለረዥም ጊዜ ህይወቱ ማሰብና መዘጋጀት አልቻለም። ያለፉት ሃያ አመታት በሙሉ የአርብቶ አደሩ ምኞት ነብሱን ማዳን እና የእለት ጉርስን ማግኘት ብቻ እንዲሆን ተደርጓል። ለዘላቂ ልማት የታሰበ ነገር ባለመሆኑ እነሆ የአንድ የዝናብ ወቅት የዝናብ ካፊያ መጥፋትን እንኳን መቋቋሚያ አቅም አጥቷል።
2. በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን የደን ጭፍጨፋና የመሬት መሸርሸር በአስደንጋጭ ሁኔታ ጨምሯል። አገሪቷ በፍጥነት ወደ ምድረበዳነት እየተቀየረች ነው።
3. ገበሬና መሬት ተለያይተዋል። አዳዲሶቹ ባለሃብቶች ለፈጣን ኪስ መሙላት እንጂ ለዘለቄታ የአፈር ልማት ፍላጎቱም፣ እውቀቱም የላቸውም። ለም መሬቶች በኢንቨስትመንት ስም በዘመኑ የወያኔ ጉልተኞች በመያዛቸውና እነሱ ደግሞ በተራቸው ለባዕዳን ቱዳሮች እየሸጡ በመሆኑ ባለሃገሩ ጭሰኝነት እንኳን አጥቶ ለቀን ሠራተኝነትና ልመና ተዳርጓል። በዚህም ምክንያት ገበሬው እንኳንስ ትልቁን የአየር መዛባት ትንሿንም የዋጋ ነውጥ መቋቋም እስከማይችልበት ደረጃ ተዳክሟል።
4. በዘር በተመሰረተ ክልላዊ ድንበር ሳቢያ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው መሥራትና ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከረሃብ መታደግ አልቻሉም። ከአንድ ክልል ወደሌላው ከተሰደደ የአገራችን አርሶ አደር ይልቅ ከቻይና ለመጣ ገበሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የእርሻ መሬት ማግኘት ይቀለዋል። እንዲያውም ኢትዮጵያዊው ገበሬ በዱላና በጥይት ሲባረር፤ የቻይናው ገበሬ ብድርና ማበረታቻዎች ይሰጠዋል።

ፋይዳ ያለው የስነ ህዝብ ፖሊሲ ባለመኖሩ የህዝብ ብዛት አሻቅቧል የመለስ ዜናዊ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን ቁጥራችንን በትክክል ሊነግረን ባይፈልግም እንኳን ረሃብ መብዛታችንን እየነገረን ነው።

**በአንፃሩ**

1. የወያኔ ቁንጮዎች ራሳቸውን ባለቢሊዮኖች አድርገዋል። በተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ጥናት መሠረት መለስና ሽሪኮቹ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ አስወጥተዋል። ይህ ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ወደ 150 ቢሊዮን ብር (ብር 150, 000, 000, 000) ይጠጋል። ይህ ገንዘብ 50, 000 የጤና ጣቢያዎችን ወይም 150, 000 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም 214, 285 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን መሥራት ያስችል ነበር። የመለስ ዜናዊ ባለሥልጣኖች በአገር ውስጥ ያካበቡት ሃብት ከላይ ከተጠቀሰው እጅግ በላይ ነው። የጥቂቶች ያለአገባብና ያለቅጥ መክበር እና የብዙሃኑን ህዝብ መደህየት፣ ችጋር ቋሚ ክስተት እንዲሆን አድርጓል።
2. አገር በቀል እና ዓለም ዓቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች የተራበውን ወገናችን ለማዳን በሚረባረቡት በአሁኑ ወቅት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ 200 ታንኮችን ለመግዛት 100 ሚሊዮን ዶላር ወጪ አድርጓል። ይህንን ራሱ መለስ ዜናዊ በትዕቢት አረጋግጦልናል። አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ከ 1.7 ቢሊዮን ብር (ብር 1, 700,000,000.00) በላይ ነው። ለታንኮቹ መግዣ በወጣው ገንዘብ 2, 428 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን መገንባት ይቻል ነበር። መለስ ዜናዊ ግን የውሃ ጉድጓዶችን ከመገንባት ይልቅ ታንኮችን ገዝቶ መታቀፍን መርጧል።

እነዚህና የመሳሰሉት ጭብጦችን በማንሳት አገራችን ውስጥ የሰፈነው ችጋር የመለስ ዜናዊ ፓሊሲ ታክሎበት እንጂ ተፈጥሮ ብቻውን ያመጣው ችግር አለመሆኑን መረዳት ይቻላል።

ህዝባችን በነፃነት ማሰብ፣ መመራመር፣ መፈተሽ ቢችል ኖሮ ረሃብን ማጥፊያ ብልሃት ማግኘት ባላቃተውም ነበር። ወደፊትም ቢሆን ተፈጥሮ እኛ እንደፈለግናት አትሆንም፤ መተማመኛችን የሰው ልጅ ወሰን የለሽ የፈጠራ ችሎታና ችግሮችን የመፍታት አቅም ነው። ለዚህ ደግሞ ችግሮችን በልጦ መገኘት ያስፈልጋል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ ሁሌ ከችግሮች በታች ሆኖ የእሱን ፈቃድ እንዲያሟላ ይፈልጋል፤ ለዚህም ነው ባርነትን ያወጀብን። መለስ ዜናዊን ከሥልጣን ሳናስወግድ ድህነትንና ረሃብ እናስወግዳለን ማለት ዘበት ነው::

በችጋር ለሚጠቃው ወገናችን መድረስ የምንችለው፤ የችጋሩ መሠረታዊ ምክንያት የሆነውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ አስወግደን ፍትህና ነፃነት የሰፈነባትን፤ ፈጠራ የተስፋፋባትን ኢትዮጵያን ስንገነባ ብቻ ነው። ጊዜ የለም .... ረሃብ ጊዜ አይሰጥም ። የወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ በአንድነት እንነሳ።

**ችጋር አንገፈገፈን፣ ረሃብ በቃን!!! በቃ!!!!!**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ የተሳሳተ ፖሊሲ የፈጠረው

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የዋጋ ጭማሪ ሃገሪቱን ለዚህ የዋጋ ግሽበት ያበቃት መሆኑን መግለጹ ታውቋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በሃገሪቱ የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገትን አስመዝግቢያለሁ እያለ የኢትዮጵያዊያንን ጆሮ እያደነቆረ በሚገኝበት በዚህ ሰአት እንዲህ አይነት ማቆሚያ የሌለው የዋጋ ግሽበት በሃገሪቱ ውስጥ መታየቱ አገዛዙ ለምእራባዊያን ሃገራት በዘፈቀደ ግምታዊ የሆነ የእድገት አሃዝን እንደማደናገሪያ እየተጠቀመ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ እንደሆነ በርካቶች ይስማማሉ።

ታዋቂ የሆኑ በርካታ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የዋጋ ግሽበት አሁን ዘረኛው ወያኔ በይፋ ካመነው አሃዝ በእጂጉ የሚበልጥ ስለመሆኑ አስረግጠው ሲናገሩ የቆዩ ከመሆናቸውም በላይ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው መስክ እየታዩ ላሉት ውስብስብ ችግሮችና ቀውሶች ተጠያቂው የዘረኛው መለስ ዜናዊ የተሳሳተ ፖሊሲ መሆኑ ብዙዎች ሲስማሙ መፍትሄውም በተባበረ ትግል ይህንን ሥርዓት በማስወገድ ብቻ እንደሚገኝ ይታመናል።

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁልፍ ቦታዎችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን ያናገራቸው የውስጥ ምንጮቻችን እንደገለጹት ቀደም ብሎ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የቴሌ ቦርድ ሰብሳቢ ሆኖ የተሾመው አርከበ እቁባይ ሲሆን የወያኔን የአሁኑን ሴራ ይበልጥ ውስብስብ ያደረገው ደግሞ ቴሌን በቀጥታ የሚያስተዳድረው የኢንፎርሜሽን ሚንስትር የሆነው ነባር የህዋሃት አባል ደብረ ጽዮን ዋሃድ ነው።

የአፈና መረቡን በማጠናከር ከፍተኛ ገቢ የሚግበሰበስበትን የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን በራሱ ታማኝ ሰዎች ሲያስዝ የኖረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገሪቷ መከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ካሉት 62 ከፍተኛ ወታደራዊ የሥልጣን ቦታዎች 58ቱን የትግራይ ተወላጆች በሆኑ የህወሃት ነባር ታጋይ ማስያዙን ከ2 አመት ተኩል በፊት የግንቦት7 ንቅናቄ ለህዝብ ይፋ ካደረገ ጊዜ ጀምሮ የወያኔ ዘረኝነት ምን ያህል አስከፊ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ከኢትዮጵያ አልፎ አለም አቀፍ ህብረተሰቡን ጭምር እያነጋገረና እየተወገዘ መሆኑ ይታወቃል።

ህወሃት በመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ካለው 62 ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች 58ቱን መቆጣጠሩ ተገቢ እንዳልሆነ የቀድሞ የህወሃት መሥራቾች እና አመራር አባላት የነበሩ ሳይቀሩ እያወገዙ ባሉበት በአሁኑ ሰዓት፤ የመለስ ዜናዊ 7ቱን ከወታደራዊ የአዛዥነት ቦታዎች አንስቶ ወደ ቴሌኮሚኒከሽን መሥርያቤቱ ቁልፍ የሃላፊነት ሥልጣን እርከን ላይ መመደብ ለህዝባችን ምን ታመጣላችሁ? የሚል የእብሪት እርምጃ እንደሆነ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አንድ የደቡብ ተወላጅ የኢሃደግ አባል ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

በሙያቸውና በዕውቀታቸው ቴሌን ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ቁጥራቸው ወደ 7 ሺህ የሚጠጋ ባለሙያዎች ያለበቂ ምክንያት ከሥራቸው ተፈናቅለው እስከነቤተሰቦቻቸው ለችጋር ሲጋለጡ የወያኔ ታማኞቹን ከወታደራዊ ተቋም አውጥቶ በሲቪል መሥሪያቤቱ መመደቡ በዚያች አገር የፖለቲካ ታማኝነት እንጂ ችሎታንና አውቀትን መሠረት ያደረገ አሠራር እየጠበበ መምጣቱን ያሳያል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

## ለሰብአዊ ክብራችንና ለነጻነታችን ስንል ግንባራችንን ሳናጥፍ እንታገላለን !!

ከዝግጅት ክፍላችን

ኢትዮጵያችን የሰው ዘር ለረጅም ግዜ የኖረባትና ጥልቅ ታሪክ ያላት ስፍራ መሆኗን መለስ ዜናዊም ያውቃል እኛም እናውቃለን። መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያችን ስሟ ገኖና ከብሮ እንድትታወቅ ስለማይፈልግ ጥልቁን ታሪክ ሸሮና በአንድ ሰው እድሜ ገድቦ አገራችንን ታሪክ አልባ ሊያደርጋት ሞክሯል።የአገራችን ታሪክ መለስ ዜናዊና እንቅልፋም ፓርላማው እንደሚያወጣው ህግ የሚደለዝና እንደ አስፈላጊነቱ የሚሻር ባለመሆኑ ሰሚ ሳያገኝ ኑሯል።

መለስ ዜናዊ የአገራችንን ታሪክ በአንድ ሰው እድሜ ሲገድበው ሊነግረን የፈለገው አንድ ነገር ብቻ ነው።ከዳተኝነቱንና ለኢትዮጵችን በጎ አመለካከት የሌለው መሆኑን።

መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እምነት የሚጣልበት ሰው አለመሆኑን ደጋግመን አይተናል። ይህ ሰው የደርግን ሥርዓት ለመጣል በረሃ በነበረ ግዜ አሉ ከሚባሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር እያበረ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ጥቅም የሚጎዳ ድሪጊት ሲፈጽም መኖሩን በርካታ መረጃዎች ያመለክታሉ።ስልጣን ላይ እስካደረሰውና እስካቆየው ድረስ ደግሞ የማይፈጽመው አስነዋሪ ነገር የለም። በአንድ ወቅት ወደ ሊቢያ ገስግሶ ሂዶ ለሙሃመድ ጋዳፊ እኛ አረቦች ነን፤ ዝርያችንም ከየመን ነው ብሎ የአገራችንን ታሪክ አዛብቶ ማውራቱን ሰምተናል። እንዲህ ማንነቱን እንደእስስት እየቀያየረ በስልጣን ወንበር ላይ መቆናጠጡ አገሪቷ በታሪኳ ከገጠሟት አሳዛኝ ክስተቶች መካከል በዋናነት ሲጠቀስ የሚኖር ነው።

በለስ ቀንቶት የሚንልክን ቤተመንግሥት ከተቆናጠጠም ቦኋላ ቢሆን ስለ ኢትዮጵያዊነት ሲጠየቅ እኔ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለትግሬነቴ ቅድሚያ እሰጣለሁ ማለቱ ህዝቡን አነጋግሮ ሳያበቃ ከወርቅ ዜር የተገኘሁ በመሆኔ እጅግ እኮራለሁ በማለት ዘረኛ አገዛዙን ለመሸከም ጀርባችንን ለሰጠነው ሚሊዮኖች ያለውን ንቀት በአደባባይ አሳይቶናል። ይህ ገና ከእንቁላሉ እንዳልተፈለፈለ ጫጩት አርቆ የሚያይ ዓይን ሳይኖረው የማይገባውን ወንበር ይዞ አገሪቷን እያመሳት ያለው ግለሰብ ምን ያላሳየው ንቀት፤ ያልሰራው ወንጀል አለ? ለዚህ ነው ይህ ግለሰብ ኢትዮጵያችንን ወደ ከፋ የጥፋት አዙሪት ውስጥ ከቶ ከማብቃቱ በፊት ከስልጣኑ መወረድ አለበት የምንለው።

እንዲህ ዓይነት ከዳተኛና ክፉ ዘረኛ ኢትዮጵያችንን ለመምራት ብርቱ የስነምባር ችግር ስላለበት ዜጎች ይህን ሰው ከስልጣን ለማውረድ በሚደረገው ትግል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ነጻነታችን ያለው በእጃችን ነው። ማንም ሰው ሊረዳን አይመጣም። ያለነው እኛው ብቻ መሆናችንን ተገንዝበን በሚያመቸን መንገድ ሁሉ እየተደራጀን ሳናፈገፍግ ለነጻነታችንና ለክብራችን የሚከፈለውን መስዋእትነት ለመክፈል ጸንቶ መታገል ዘመኑ የሚጠይቀን ግዳጅ ነው።

መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ የመቆየት ዘመኑ እየረዘመ በሄደ ቁጥር የአገሪቷ ችግር ከምን ግዜውም በላይ እየተወሳሰበ እንደሚሄድ ዜጎች ጠንቅቀው ሊረዱት ይገባል። ይህ ግለሰብ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ከብሄራዊ ስሜት ይልቅ ጎሰኛነት ሥር እየሰደደ ይሄዳል። ጎሰኝነቱን ተከትሎ የሚመጣው አድሎ፤ ዝርፊያና ጥላቻው ከመቸውም በላይ የከፋ ይሆናል። ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነው ብዙሃኑም ጥቂቶችን ተሸክመው ስቃያቸው በዝቶ የሚኖሩበት የመከራ ዘመንም ይበዛል። ይህ ግለሰብ ሥልጣን ላይ እስከቆየ ድረስ ርሃቡ እርዛቱና ስደቱ በሥፋት ይቀጥላል።

መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ነጻነት፤ ፍትህ፤ የህግ የበላይነት፤ ሰብዓዊ መብት የሚባሉ ፈጣሪ ለሰው ልጆች ያበጃቸው በጎ ነገሮች ሁሉ በአገራችን አይኖሩም። እንዲያውም እነዚህን የፈጣሪ ስጦታዎችን መጠየቅ መለስ ዜናዊ እስካለ ድረስ ወንጀል እንደሆነ ይቀጥላል። ከተራ ወንጀልነትም አልፎ በአሸባሪነት አስከስሶ የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ ይሆናል።

ለዚህም መለስ ዜናዊና እንቅልፋም ፓርላማው በኢትዮጵያ ውስጥ "የዘግነት መብትን መጠየቅ" አሸባሪነት ነው በማለት ፍርጀዋል። ፈጣሪ ሰው አድርጎ የፈጠረን እርሱ የሰጠንን በጎ ስጦታ ተጠቅመን እርሱን አመስግነነው ደስ ብሎን እንድንኖር እንጂ መለስ ዜናዊ ሰው የመሆን ሚስጢራችንን በተፈታተነን ቁጥር እያማረርን እንድንኖር አይደለም። ሰው ከሌሎች እንስሶች የሚለየውም እነዚህ ከፈጣሪ የተሰጡትን ስጦታዎች ማወቁና በአግባቡ መጠቀም መቻሉ ነው። በኢትዮጵያችን ውስጥ ሰው እንሆናለን ያሉ ዜጎች ላይ የሚደርሰውን እያየንና እየሰማን ዝም ማለት አይገባንም። ሰው መሆናችን ይታወቅልን ያሉ ዜጎች ሲታሰሩ፤ ሲደበደቡ፤ ተገድለው ሜዳ ላይ ሲጣሉና ለስደት ሲዳረጉ አይቶ እንዳላዩ መሆን አስተዋይ ህሊና የሚፈቅደው ሥራ አይደለም። ሰው የሚያሰኘንም እንዲህ ዓይነት ግፍ በገዛ ወገኖቻችን ላይ ሲፈጸም አይተን ዝም አለማለታችን ነው።ከበግና ከበሬ የምንለየውም እንዲህ ዓይነቱን ግፍ በቃ ማለት ስንችል ነው።

የሰሞኑ እሥራትና አሳፋሪ ክስ ሰው ስለመሆን ጥያቄ የተሰጠ መልስ ነው። የአውራባው ታይምስ ምክትል አዘጋጅ ጋዜጤኛ ውብሸት ደምሴ፤የፍትህ ጋዜጣ አምደኛ ርእዮት ዓለም፤ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓሪት መሪዎች እነ አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚዝብሄር፤ አቶ ደጀኔ ተፈራና ሌሎችም ብዙ ዜጎች ከያሉበት ተይዘው በአሸባሪነት ክሥ ተመስርቶባቸዋል። የእነዚህ ዜጎች ወንጀል አንድ ነው። ሰው መሆናችን ይታወቅ መብታችንም ይጠበቅ ማለታቸው ነው ወንጀላቸው።

መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ በተፈጥሮ ያገኘነውንና ከፍጥረታት ሁሉ የሚለየንን ሰው የሚያደርገንን መብት ለማስከበር መቆም አሸባሪነት ነው።ጋዜጠኛ ውብሸት ደምሴ ስለስውነቱና ሰው ስለሚያደርገው መብት በመጠየቁ ታሰረ ተደበደበ በአሸባሪነት ተከሰሰ። ወጣቷ ጋዜጤኛ ርእዮት ዓለምም እንዲሁ በተመሳሳይ ምክንያት በመለስ ጸጥታ ኃይሎች ተያዘች ታሠረች በአሸባሪነት ተከሰሰች።ሌሎችም እንዲሁ ከያሉበት ተያዙ ታሠሩ በአሸባሪነት ተከሰሱ። በንዲህ ዓይነት ሁኔታ አገሪቷ ሰው አልባ ሁና የቀበሮዎችና የተኩላዎች መፈንጫ እስከምትሆን ድረስ ሰው ነኝ ብሎ ተፈጥሮ ለለገሰቺው ስብአዊ ክብር ተቆርቋሪነት ያሳየ ሁሉ ወደ ወህኒ መጋዙና ሃበሳውን መቁጠሩ ይቀጥላል።

የመለስ ዜናዊ ዓላማ የተደበቀ አይደለም።ዓላማው አገሪቷን ሊመራ የሚችል በጥበብ ያደገ፤ ለአገሩ ታማኝ የሆነ፤ ቅንና፤ ከአድሎ የጸዳና ለእውነት ግንባሩን ሳያጥፍ ሊቆም የሚችል ትውልድ እንዳይፈጠር ማድረግ ነው።ዜጎች እንደ ሰው ልጅ ከማሰብ ይልቅ እንደ በግና በሬ ሣሩን ብቻ እያዩ ይኖሩ ዘንድ የመለስ ዜናዊ ምኞት ነው። በመለስ ዜናዊ አስተሳሰብ ዜጎች የአገራቸው ባለቤት አይደሉም። አየሩም፤ ወንዙም፤ ጋዜጣውም፤ ሬዲዮኑም፤ ቴሌቭዥኑም፤ ተራራውም፤ ህዝቡም የንጉስ መለስ ዜናዊ ሁኗል። እርሱ ያልወደደውን ለማጥፋት እንደ ሰጋር በቅሎ ጭኖ በሚጋልብበት ፓርላማ አማካኝነት ህግ ያወጣል። በዚህም ህግ መሠረት ወጣቶች፤ ጎልማሶችና አዛውንቶች በሙሉ ወደ ሞት ሰርጥ ይጋዛሉ።

ይሄ መብቃት አለበት። እየንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰው እንጂ በግና በሬ አይደለም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደ ሰው መኖር እንዳይችል በመለስ ዜናዊ ክብሩን ተነጥቆ ተዋርዶና በፍርሃት አረንቋ ተውጦ እንዲኖር መደረጉ መብቃት አለበት። ይህን ውርደት ከበቂ በላይ ተሸክምነዋል አሁን ግን በቃ ሊባል ሁኔታው ግድ ይለናል።

ኢትዮጵያዊ እንዲህ ብናገር ምን ይደርስብኝ ይሆን ብሎ ማንንም ሳይፈራ የልቡን በፈለገው መንገድና ቋንቋ መናገር መብቱ ነው።ኢትዮጵያዊ የቀበሮዎችና የተኩላዎች መፈንጫ በሆነች አገር ውስጥ ሳይሆን የህግ የበላይነት የተከበረባትና የሰው ልጅ መኖሪያ በሆነች አገር ውስጥ ለመኖር ተኩላዎችና ቀበሮዎች ሊያቆሙት አይገባም። ኢትዮጵያዊ ሃያ ዓመት በጫንቃው ላይ እንደመዥገር ተጣብቆ የሙጥኝ ብሎ ደሙን ከሚመጠው ዘረኛ ገዢ ተላቆ በተወሰነ ግዜ የሚሾመውና የሚሽረው መሪ እንዲኖረው ለማድረግ ከማንም የሚያንስ ህዝብ አይደለም። ኢትዮጵያዊ መሪውን ለመምረጥ ብቻ ሳይሆን ራሱም አገሩን መርቶ የሰው ልጆች የደረሱበት ለማድረስ ቅንነቱና አርቆ አስተዋይነቱ ያለው ህዝብ ነው። መለስ ዜናዊ ግን ገና ለዚህ ቁም ነገር አልበቃችሁም ብሎ በአቋሙ ጸንቷል። ይህ እኩይ ሃሳቡ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሊቆጨውና ሊያበሳጨው ይገባል።ሰው መሆን ማለትም እንዲህ አይነቱን ንቀትና ውረድት አልቀበልም ማለት ነው።

በመጨረሻም እንደዜጋ ለስብአዊ ክብራችንና ለነጻነታችን ያለንን ዋጋ በማራከስ በመሳሪያ ሃይል አፍኖና ገዝቶ እስከወዲያኛው ሊጋልበን የሚሻውን ዘረኛውንና ዘራፊውን መለስ ዜናዊን ከስልጣን ማባረር ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም። ይህንንም ለማድረግ እኛን ሊረዳ የሚመጣ ማንም እንደሌለ አውቀን ሳናፈገፍግ ለነጻነታችንና ለክብራችን ስንል ጸንተን እንታገል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

## በአለታ ወንዶ ብጥብጥ ተከሰተ፣ ወጣቶች ወያኔ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢሳት እንደገለጸው ሁለት ሺህ የሚሆኑት እወጣቶች በቀጥታ ወደከተማው በመግባትና ድንጋይ በመወርወር አለታ ወንዶ ከተማን እንዳናወጡአትና፣ በአጸፋው ፖሊስ ተኩስ በመክፈት፣ ሁኔታውን በቁጥጥር ስር ለማዋል እንደሞከረ የታዋቀ ሲሆን ከግጪቱ ጋር በተያያዘ 32 ወጣቶችን መታሰራቸው ታውቁአል።

ይህ ግጭትም በአጎራባች ወረዳአዎች በአሮሬሳና በበንታ ሊቀጣጠል እምንደሚችል መገመቱን የገለጸው ኢሳት፣ የዚህ አይነት ስብሰባ በየተመሳሳይ በይርጋለም ከተማ እየተካሄደ እንደሆነና በይርጋ አለም ለተገኙት ተሳታፊዎች በቀን ሃምሳ ብር የተከፈላቸው መሆኑ ታውቁአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በተለያዩ መንገዶች የመከፋፈልና የማበጣበጥ ስራ ሲያከናውን የቆየና በማከናወን ላይ ያለ መሆኑም በሰፋት የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚሁ በተጨማሪ እጂግ በርካቶችን በገንዘብና ጥቅማ ጥቅም የመደለል ስራ በስፋት ይሰራል። ይሁን እንጂ ዜጎች ላለባቸው ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግር ዘረኛው ወያኔ የሚሰጣቸውን ገንዘብ ሙያ በልብ ነው በማለት ይቀበሉ እንጂ ለዘረኛው የወያኔ አግዛዝ ልባቸውን የሰጡበት ጊዜ እንደሌለ በስፋት ሲዘገብ ቆይቱአል።

## "ቪ.ኦ.ኤ. የተቃዋሚዎቼን አስተያየት ከማሰራጨት እንዲታቀብ ይደረግልኝ" ሲል የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለአሜሪካ መንግሥት ያቀረበውን ጥያቄ ለህዝብ ይፋ ያደረጉት የአፍሪካው ቀንድ ሃላፊ ከስልጣናቸው መነሣታቸው ታወቀ

በቅርቡ የባራክ ኦባማ አስተዳደርን በመወከል ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ የነበረው የአሜሪካ ድምጽ አስተዳደር ቦርድ ልዑካን ቡድን፤ ከበረከት ስምዖን ጋር ባደረገው ውይይት " የቪኦኤ የተቃዋሚዎችን አመለካከት መዘገቡን ካላቆመ ምንም አይነት ትብብር አየደረግለትም" መባሉን ለህዝብ ይፋ ያደረጉት የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአፍሪካ ቀንድ ሃላፊ ሚስተር ዴቪድ አርኖልድ፤ ይፋ ባልሆነ ዉይይት የተነገራቸዉን መረጃ አየር ላይ አውለዋል በሚል ክስ ከነበሩበት የሃላፍነት ቦታ መነሳታቸውን አዲስ ቮይስ የተባለው ድህረ ገጽ አስታወቀ።

የአፍሪካ ቀንድ ሃላፊ የነበሩት ዴቪድ አርኖልድ ከልዑካን ቡድኑ ጋር አዲስ አበባ በነበሩበት ወቅት የመለስ ዜናዊ አፈቀላጤ የሆነው በረከት ስምዖን የወያኔው አገዛዝ በቪኦኤ ላይ እንዳይቀርቡ በማለት የጠየቃቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ያጋለጡ ባለስልጣን ሲሆኑ 7 አባላት ከነበረው የአሜሪካ ድምጽ የአስተዳደር ቦርድ ልዑካን ቡድን ጋር በመሆን በኢትዮጵያ፤ በናይጀሪያ እና በደቡብ ሱዳን ተዘዋወረዉ የሥራ ጉብኝት አድረገው የተመለሱ ናቸው።

ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በመጣው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች ምክንያት ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል በማለት በከፍተኛ ፍርሃትና ስጋት ውስጥ ያለው የመለስ አገዛዝ በአሜሪካ ድምጽ እንዳይቀርቡ በማለት ከጠየቃቸው ሰዎች መካከል ፕሮፌሰር ፓዉሎስ ሚልኪያስ፤ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፤ ዶ/ር መረራ ጉዲና፤ ፕሮፌሰር ጌታቸዉ መታፈሪያ፤ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ ግርማ ሞገስ፤ ስዬ አብርሃና የኤርትራዉ የማስታወቂያ ሚኒስትር አሊ አብዶና ሌሎችም እንደሚገኙበት ሚስተር ደቪድ መናገራቸው ይታወሳል።

ባለስልጣኑ ሚስተር ደቪድ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር ጁን 23 ቀን የሰጡትን መረጃ የዘገበው የአመሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማሪኛው ዝግጅት ክፍል ዜናው ተላልፎ ካበቃ ጥቂት ቀናት ቦኋላ በጽሁፍም ሆነ በድምጽ ድህረ ገጹ ላይ አስቀምጦት የነበረውን ፋይል ማንሳቱ ብዙዎችን ሲያነጋገር ስንብቶአል።

ይህንን አስመልከቶ የአሜሪካን ድምፅ የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ዴቪድ ቦርጊዳ ለአዲስ ቮይስ ድረ ገፅ ጋዜጠኛ አበበ ገላዉ በላኩት ኢሜይል በዜናዉ ላይ የተደረገ ሳንሱር እንደሌለ ገልፀዉ ዜናዉ ከሬድዮ ጣቢያዉ ድረ ገፅ ላይ እንዲነሳ የተደረገዉ በአዲስ አበባ ከተደረገዉ ዉይይት የተዛባ ትርጉም በማምጣቱ እንደሆነ አመልክተዋል። ሆኖም የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተሩ የአፍሪካው ቀንድ ሃላፊ ከሃላፊነታቸዉ ስለመነሳታቸዉ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል።

የረዢም ጊዜ አገልግሎት ያካበቱት ዴቪድ አርኖልድ ከሃላፊነታቸዉ መነሳታቸዉ እራሱን የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ተላላኪ ባደረገዉ የኢትዮጵያ አምባገነን መንግሰት አቤቱታ መሰረት ከሆነ ጉዳዩ በቀላሉ ሊታይ እንደማይችልና ህጋዊ ተቀባይነት እንደማይኖረዉ አልፎ ተርፎም ብዙ ሊያዳርስ እንደሚችል ኢትዮጵያዉያን የህግ አዋቂዎችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እስከመጨረሻዉ የሚገፉበት አጋጣሚ መሆኑን ከወዲሁ በመናገር ላይ ናቸዉ።

## የወያኔ የሽብርተኝነት ህግ ድምበር ዘለለ፤ ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ህግ ሊከሰሱ ነው

ቀደም ብሎ በዜና ዘገባቼን የገለጽነውና በኦጋዴን ክልል በኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባርና በኢትዮጵያ ዘረኛ አገዛዝ መካከል ያለውን ጦርነት ለመዘገብ ወደ ክልሉ ያመሩትና በዘረኛው ወያኔ ወታደሮች በጥይት ተመትተው ለእስር የተዳረጉት ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች በሽብረተኝነት ህግ ክስ እንደሚመሰረትባቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ የሆነው ሆድ አደሩ ዲና ሙፍቲ መናገሩን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ጋዜጠኞቹ እስካሁን ፍርድ ቤት ገና ያልቀረቡ ሲሆን በአዲሱ አዋጅ ተብየው መሰረት ያለምንም ክስ እስከ አራት ወር ሊታሰሩ የሚችሉ ሲሆን ተከሳሾቹ በሚሸረብባቸው ሴራ በፍርድ ቤት ተብየው ጥፋተኛ ናቸው ከተባሉ ከ20 አመት እስከ እድሜ ልክ ሊደርስ የሚችል እስራት ሊፈረድባቸው እንደሚችል ታውቋአል።

በሌላ በኩል ኤ.ኤፍ.ፒ እንደዘገበው የስዊድን አምባሳደር ጋዜጠኞቹን መጎብኘታቸው የታወቀ ሲሆን የስዊድን መንግስት የልኡካን ቡድንም ወደ ኢትዮጵያ በመጓዝ የዘረኛውን መለስ አገዛዝ ባለስልጣናት ሊያነጋግር እንደሚችል ታውቋአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ አገዛዙን በሚቃወሙና በተለይም በሃገሪቱ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ዘግናኝ ግፍ ለዓለም ህዝብ በማጋለት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊያንንም ሆነ ሌሎች የውጪ ሃገር ዜጎች የሚፈልገውን ስምና ታፔላ በመለጠፍ የሚችለውን ሲያስርና ሲገርፍ፣ የማይችለውን ደግሞ በየአደባባዩ ሲዘልፍ መቆየቱ በበርካታ የመገናኛ ብዙሃን ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

በተያያዘ ዜና እነኚህ ስዊድናዊያን ጋዜጠኞች ከእስር እንዲፈቱ አለማቀፍ ግፊት በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ እንዲደረግ ጥሪ ያቀረበ ሲሆን ኦብነግ እንደሚለው ጋዜጠኞቹ ሊያዙ የቻሉት የፑንትላንድ መንግስት መረጃዎችን ለዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በማቀበሉ መሆኑ ታውቋአል።

የወያኔው አገዛዝ 15 የኦብነግ ወታደሮችን ገድያለሁ ብሎ ማስታወቁ ፍጹም ሀሰት ነው የሚለው ኦብነግ፣ ግለሰቦችን አጅበው የሄዱት 4ቱ መንገድ መሪዎች ሲቪሎች ሲሆኑ አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ወታደሮች በጅምላ ሳይገድሉአቸው እንዳልቀሩ ተናግሯል። ኦብነግ እንደገለጸው ጋዜጠኞቹ ተገደሉት የድርጅቱ ታጋዮች ወደ ሚገኙበት አካባቢ ሳይደርሱ እንደሆነም ታውቋአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በ ኦጋዴን አካባቢ ያለውን ከልክ ያለፈ በደልና ስቃይ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቁአማት እንዳይታዘቡ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጂቶች በአካባቢው እንድይታዩ የከለከለ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ የስዊድናዊያኑ ጋዜጠኞች መታሰር ደግሞ ሌሎች ጋዜጠኞች የኦጋዴንን ችግር እንዳይዘግቡ አስቀድሞ ለማሸማቀቅ የተወሰደ እርምጃ ነው የሚለው ኦብነግ፣ የአለማቀፍ ጋዜጠኞች ወያኔ የሚያቀርበውን ፕሮፓጋንዳ ባለመስማት ከጋዜጠኞች ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ማቅረቡ ታውቋአል።

## ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ግቡን እንዲመታ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከምንም በላይ አንድነት ከሀገር ፍቅር ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ስሜት እንዲኖር ያስችላል፡ ያሉት ዶ ር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያዊነት መሰረት ዜግነት መሆኑን ገልጸው መብትን የሚያከብር መንግስት በሌለበት ዜግነት ትርጉም እንደሌለውና አንድነትም እየላላ እንደሚመጣ መናገራቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል። ዶር ብርሃኑ ነጋ በመጨረሻ ማንም ቢሆን ፍትህን ሳያስከብር፡ዲሞክራሲያዊ መብትን ሳያረጋግጥና እኩልነትን ሳያስጠብቅ ስለአንድነት ማሰብ ፈጽሞ አይቻልም ካሉ በኋላ፡ የኢትዮጵያ አንድነት ከተከላካይ ብሄርተኝነት የሚላቀቀው ፍትህ፡ ዲሞክራሲና እኩልነት ሲሰፍኑ ብቻ ነው በማለት ንግግራቸውን ማብቃታቸው ታውቋል።

በሌላም በኩል የኦነግ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል እና የግንባሩ የሕግ ክፍል ሃላፊ የሆኑት ዶክተር ኑሩ ደደፎ የድርጅታቸውን የወደፊት ስትራቴጂ በስፋት ካቀረቡ በኋላ የዘረኛው መለስ አገዛዝ 20 ዓመታት በስልጣን ለይ የቆየው የመከፋፈል ስትራቴጂን በመጠቀም እንደሆነና ይህም በተቃዋሚ ሃይሎች ትብብር ሊሰበር እንደሚገባው ገልጸዋል፣፤ ዶ ር ኑሩ ቀጥለውም ኦነግ ከምንጊዜውም በላይ ለትብብር መዘጋጀቱንና በዚህም የወያኔ ኢህአዴግን ዘረኛ አገዛዝ ለማስወገድ ድርጂታቸው ስትራቴጂ መንደፋን ይፋ አድርገዋል።

በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር የሚደረገው ትግል ፍትህንና እኩልነት የሚያመጣ እስከሆነ ድረስ ኦነግ ላለመተባበር ምንም ምክንያት የለውም ያሉት ዶክተር ኑሩ ደደፎ ፣ በእያንዳንዱ ህዝብ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃና ግፍ በሁላችንም ላይ እንደደደረሰ በመቁጠር በአንድ ላይ ከተነሳን የግፈኛው መለስ አስተዳደርን ለመጣል በጣም ቀላል ነው ሲሉ መናገራቸውን ሪፖርተራችን ገልጿል።

ዶክተር ኑሩ አብዛኛው ሰው በኦነግ ላይ ያለውን ጥርጣሬ እንዲያስወግድ ከጠየቁ በኋላ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ብቻውን ሊሆን እንደማይችል ከተወያየና በውስጡ ማሻሻያዎችን ካደረገ በኋላ የወያኔ ኢህአዲግን አገዛዝ ለማስወገድ ከሚታገል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ድርጅት ጋር በአንድነት ለመስራት ውሳኔ ማስተላለፉን ለስብሰባው ተሳታፊዎች ገልጸዋል። አያይዘውም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የሰሜን አፍሪካው ዓይነት የህዝብ ቁጣ በኢትዮጵያ ውስጥም እንዲቀጣጠል ከሌሎች ሃይሎች ጋር በቅንጅት እየሰራ እንደሆነም አረጋግጠዋል።

ከወያኔ ኢህአዲግ አገዛዝ መወገድ በኋላ የሽግግር መንግስት ማቋቋምና በህዝብ የተመረጠ መንግስት እንዲመሰረት ማድረግ የኦነግ ዓላማ ነው ሲሉ የገለጹት ዶክተር ኑሩ ፣ ጊዜው የትብብር ነው፡ ከዚህ በኋላ የማንከፋፈል መሆናችንን አረጋግጠን ልንታገል ይገባል በማለት መልዕክታቸውን ማስተላለፋቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

በዚሁ ስብሰባ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት ኢትዮጵያዊው ታዋቂ ኢኮኖሚስት ዶክተር ጌታቸው በበኩላቸው በተለይ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ወደ ትብብሩ መምጣቱ ለቀጣይ ትግል አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩ ሲሆን ኦነግን ያገለለ ትግል ብዙም እንደማያስኬድና እንዲህ ዓይነቱ መድረክ ተጠናክሮ ከቀጠለ ማዶ ለማዶ የተራራቁ ግን ለአንድ ዓላማ የሚታገሉ ድርጅቶች ተቀራርበው እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው ማለታቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

ወጣቱ ትውልድ ወደትግሉ በመምጣት ትግሉን የመምራቱ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት አድርገው የተናገሩት ዶክተር ጌታቸው፣ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወጣቶች ትግሉን እየመሩት መሆናቸውን በስፋት እያስመሰከሩ ነው ካሉ በኋላ በበቃ እና በኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅናቄ የተጀመረው የወጣቶች የትግል መነሳሳት ሊደገፍና ሊጠናከር እንደሚገባም በመግለጽ ንግግራቸውን አጠቃለዋል።

በእለቱ በተካኄደው የኢትዮጵያዊያን ስብሰባ ሰፊ የሆነ የጥያቄና መልስ ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ በአርቲስት እና አክቲቪስት አበበ በለው አማካኝነት ኦጋዴን ውስጥ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ርሃብ የሚያሳይ የ8 ደቂቃ ፊልም ታይቷል።

ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታዳሚ የተገኘበት ይህ ስብሰባ በአጠቃላይ ከ4 ሰዓታት በላይ የፈጀ ሲሆን፤ የዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ዋና አስተባባሪና የጥምረት ጸሀፊ የሆኑት አቶ ነዓምን ዘለቀ መሰል ስብሰባዎችን በየሶስት ወሩ ለማካሔድ መታቀዱን ከገለጹ በኋላ ስብሰባው መጠናቀቁን ዘጋቢያችን ገልጿል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org